# የኢሕአፓ 36ኛ ዓመት በዓል በኖርዌይ፥

በኖርዌይ ኦስሎ ከተማ የሚገኙ የኢሕአፓ (EPRP) አባላትና ደጋፊዎች ድርጅቱ የተመሠረተበትን 36ኛ ዓመት በደማቅ ሁኔታ ዛሬ ሰኔ 5 ቀን አከበሩ ።

በዓሉን በትግሉ ሂደት ላይ የተሰዉትን ቁርጥ የድርጅቱን ልጆች በ 1 ደቂቃ የህሊና ፀሎት በማሰብ የከፈቱት አቶ ጌትነት ውብሸት የቀደምት የድርጅቱን ታሪክና ያሳለፈዉን ውጣ ውረድና አሁን የደረሰበትን ደረጃ በዕለቱ ከተገኘዉ ከ70 በላይ ለሚሆነው ታዳሚ አቅርበዋል ።

አቶ ጌትነት አያይዘውም በድርጅቱ ውስጥ የአንጃዎች መፈጠር እጅግም የማያስገርማቸው መሆኑን ገልፀው በድርጅቱ ታሪክ ሶስትኛ ጊዜው መሆኑና ሁሉም ተንኮታኩቶ ሲወድቅ የታየና የሚታይ መሆኑን ጠቁመዋል በተጨማሪም በተላያዩ ጊዜያት የተከሰቱት የአንጃ እንቅስቃሴዎችን የሚያመሳስላቸው ሁሉም አጎንባሽ፣ ትግል አምካኝ በታኝና በድርጅት ጀርባ የተደራጁ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በዕለቱ በድርጅቱ ውስጥ ያካበተ ዓመታትን ያስቆጠሩትና በስደት ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩት አቶ ታደሰ ገብረሚካኤል የስሻል ዲሞክራሲና ሊበራል ዲሞክራሲ በቲዎሪ ደረጃ ከምዕራባዉያን የተለያዩ አገሮች ተመክሮ ላይ ጥናትን የዳሰሰ አጠር ያለ ትምህርትን ሰጥተዋል።

በዚሁ በርካታ የሆኑ ወጣቶች በተሳተፉበት በዓል ላይ ዶክተር ሀብታሙ አቤ የሴቶችና የወጣቱ ሚናና ድርሻ ላይ ሰፋ ያለ ገለጻ ሰጥተው ኢሕአፓ የነገ ብሩህ ተስፋ የሚል ዓርማ ለድርጅቱ የወጣቶች ተወካይ ለአቶ አበባው ተክለብርሃን አስረክበዋል።

የዕለቱን ፕሮግራም የመሩት አቶ አሳየኸኝ ይህ አገራዊ ኮሚቴ ያዘጋጀው የዛሬውን በዓል ካለፉት ለየት የሚያደርገው በቁርጠኛ ኢትዮጵያዊነት የሚታገለው ድርጅታችን ተሞክሮበት የነበረዉን የአንጃ ጥቃት በድል ተወጥቶ ለቀጣዩ ጉዞው የመንፈስ ማነቃቃት የአንድነት ስሜቱን መጠበቂያ እንደሆነ ገልጸው ለዝግጅቱ መሳካት ክፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱት የተግባር፣የወጣትና የሴቶች ኮሚቴዎች ከፍ ያለ ምስጋና አቅርበዋል።

ከዕለቱ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናኙ የስነ ግጥም ስራዎች በጋዜጠኛና ጸሐፊ አቶ ያሬድ ተሾመ የቀረበ ሲሆን በአዝናኝ የብሔር/ ብሔረሰብ ሙዚቃዎች በዓሉን አድምቀውት ውለዋል።


Carlsberg
Carlsberg


ETHIOPIA:



